የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

Ministry of Foreign Affairs
of Ethiopia

# የዳያስፖራ አባላት በአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ በኮንስትራክሽን፣ ኢንዱስትሪ እና በቤት ልማት ዘርፎች ሊሳተፉና ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸው መስኮች

## I. በአነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ዘርፍ ሲሳተፉና ተጠቃሚ ሲሆኑ የሚችሉባቸው መስኮች፣

### የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ

- በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት በተለያዩ የሽመና ፣የፋብሪካ ጨርቆች፣የተዘጋጁና ለምዕራቡ ዓለም በቀለምና በወቅት ፍላጐት ተስማሚ ሆነው የሚዘገጁ ልብሶችን ማቅረብ፣
- የቆዳ ውጤቶች ምርት በተለይ በጫማና በጫማ ሶል፣ በቆዳ አልባሳት፣ በቆዳ ቦርሳ፣ ሻንጣ፣ የስፖርት ትጥቅና ቁሳቁስ ማቅረብ፣
- የሹራብ ምርቶች ካልሲዎችና የሹራብ ክሮች ማምረት፣ የተለያዩ የብርድ ልብስ ዓይነቶችና ጃንጥላዎች ማምረት፣

### የምግብና መጠጥ ዘርፍ

- ጥሬ ዕቃችን (ቦለቄ፣ሽንብራ፣ምስር፣አተር...) በማዘጋጀት በእሽቱ በማሸግ ቢቀርብ (ከገበሬዎች ጋር በተቀናጀ አሠራር) ሰፊ ገበያ ይኖረዋል፣
- አትክልትና ፍራፍሬ አቅርቦት እያደገ በመሄድ ላይ በመሆኑ በምርቱ ላይ እሴት በመጨመር ( በመጭመቅያና በማሸግ) ማቅረብ፣
- ቡና፣ ቅመማ ቅመም፣ ማር፣ቲማቲም፣በተለያዩ መልክ በማዘጋጀት በማሸግ ለገበያ ማቅረብ፣
- የባህል መጠጦችም በዘመናዊ መልክ በማጣራት በመቀመምና በማሸግ ማቅረብ፣
- የታሸጉ የጤፍ ዱቄት፣የቆሎ፣የበሶ፣የዳቦ ቆሎ፣ የቺፕስ፣ የአዋዜ ወዘተ ... ማዘጋጀት ለገበያ ማቅረብ፣
- የተለያዩ የከረሜላ የቼኮሌት የማስቲካ ምርቶችን በማምረት የገቢ ምርቶችን መተካት፣

### የከተማ ግብርና ዘርፍ

- ዘመናዊ የወተት እርባታ በማከናወን የተለያዩ የወተት ተዋጽኦችን ለገበያ ማቅረብ
- ዘመናዊ የዶሮ እርባታዎችን በማካሄድ ሰፊ የገበያ እድልን በሀገር ውስጥና ለአካባቢ አገሮች ማቅረብ
- በከተሞችና በገቤሬው አካባቢ ለሚካሄደው የእንስሳት እርባታ የሚያገለግል የእንስሳት መኖ አዘጋጅቶ ማቅረብ
- በዘመናዊ ሆቴሎችና በከተማው ህብረተሰብ ተፈላጊ የሆነው የእንጉዳይ ምርት አምርቶ ማቅረብ (በተለይ ለአዲስ አበባ ከተማ ተጠቃሚዎች)

### ለትምህርት ሥራ የሚውሉ ቁሳቁሶች ምርት

- የተማሪች ቦርሳች (ከሸራ፣ጨርቅ፣ፕላስቲክ፣ናይለን ) የተሰሩ በማምረት እያደገ የመጣውን ፍላጐት ማሟላት
- የትመህርት መሣሪያችና ቁሳቁስ እርሳስ ላጲስ መቅረጫ ማስመሪያ ኮምፓስ ደብተሮች ፓዶች ፎልደሮች አዘጋጅቶ ማቅረብ፣

### የቱሪስት መስህቦችንና ባህላዊ እሴቶችን የሚያስተዋወቁ ምርቶች

- ባህላችን ኑሮቸችንና ቅርሶቻችንን የሚያስተዋዉቁ ከጨርቅ፣ ከነሐስ፣ መዳብ፣ ብር፣ ወርቅ፣ እንጨትና ፕላስቲክ የሚሰሩ ቁሳቁሶችን ፣
- በቅርጻ ቅርጽና በአሻንጉሊት መልክ የሚዘጋጁ የሸክላ የእንጨት የጨርቃ ጨርቅ ምርቶች ማቅረብ
- ባህላዊና የብሔር ብሔረሰብ ልብሶችን በዘመናዊ ጥበብ በማዘጋጀት የሚቀርቡ የቱሪስት ቁሳቁሶች ማምረት

### የእንጨት ሥራ ዘርፍ

- የቀርከሀ ምርትን በተለያዩ የቤት የቢሮና የህንጻ አገልግሎች በሚውሉ ምርቶች በመቀየር ለገበያ ማቅረብ
- ከውጭ የሚገቡ የቤትና የቢሮ ዕቃችን በማምረት መተካትና ለሀገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ
- የእንጨት ማሸጊያና ማጥበቅያ ሙጫችን ማምረትና ገቢ ምርቶችን መቀነስ
- በደን ተከላ በመሳተፍ ለጣውላ ኮምፖርሳቶ ችፕውድ የሚሆን ማምረትና ማዘጋጀት

### ለገበሬው የሚያገለግሉ መሣሪያችና መገልገያች

- ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ አነስተኛ ሞተሮችን መፈብረክ ወይም መገጣጠም
- በየገጠሩ ከውጭ የሚገቡትን ሊተኩሉ የሚችሉ የእህልና የበርበሬ ወፍጮች እና ማበጠሪያች መፈብረክ
- ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ ፕላስቲክ ፓይፖችን ማምረት
- ለግብርና ሥራ የሚያገለግሉ የምርትና የትራንስፖርት መሣሪያች (ማረሻች ጋሪች ወዘተ) ማምረት

### የመአዛ ዘይት የማዘጋጀት ሥራ

- የሽቶ እና ለውበት ማስዋብያ የሚሆኑ የመዓዛ ዘይቶች ማምረት
- ለምግብ ጣዕምና ለመድሀኒት የሚሆኑ የመአዛ ዘይቶችን ከገበሬው ጋር በመቀናጀት ማምረትና ጨምቆ ማቅረብ

### የውድቅዳቂ ወይም የትርፍ ምርት ሥራዎች

- ከውድቅዳቂ ፕላስቲኮች ወረቀቶች ጨርቃጨርቅና ጠርሙስ ወዘተ ምርቶችን መልሶ ማምረትና በዚያውም የከተሞችን ንጽህና መጠበቅ

### የወርክሾፕ አገልግሎቶች

- ከፍተኛ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃች ጥገና አገልግሎት መስጠት
- metal casting ,metal treatment, galvanizinge, electro plating ,foundry ሥራች ላይ መሳተፍ
- የተለያዮ ማሽኖች ማለትም የዳቦ መጋገሪያ የድንጋይ ወፍጮች mixers ,vibrators በሀገር ውስጥ ማምረት

## II. በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ቢሳተፉ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚሉባቸው መስኮች

### ➢ በተለያዩ የግንባታ ዘርፎች በሥራ ተቋራጭነት መሳተፍ

- ከፍተኛ አቅም የሚጠይቁ ግንባታዎች ላይ በልዩ ልዩ ሙያ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት መሳተፍ
- በመንገድ በባቡር በመስኖ ወዘተ ባሉ የግንባታ ዓይነቶች ላይ በአማካሪነት መሳተፍ
- የሀገራችን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን ለማሳደግ በተለያዩ ወጪ እና ጊዜ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች ሽግግር እንዲፈጠር ማድረግ

### ➢ በኢንዱስትሪ ውጤቶች እና የአካባቢ ግብዓት ምርትና አቅርቦት

- የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን (ዶዘር ግሬደር ሎደር ወዘተ )በማስገባት ለኪራይ እንዲዉሉ ማድረግ
- የውጭ ባለሀብቶችን በኮንስትራክሽን ዘርፍ በመሳብ በጋራ በመሆን በወጭ ምንዛሬ አቅርቦቱ መሳተፍ
- ለግንባታ ሥራ የሚያገለግሉ የስካር ፕሮፕስ አቅርቦትና የኪራይ አገልግሎት መስጠት
- ለግንባታ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኘውን ኮንክሪት ባቺንግ ፕላንት በማምጣት ኮንክሪት ማምረት

## III. በቤት ልማት ዘርፍ ቢሳተፉና ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉባቸው መስኮች

- ለመኖሪያ እንዲሁም ለምርትና አገልግሎት መስጫ ስራ ዎች በተዘጋጁ ቦታዎች ቤት ለመገንባት የሚያስፈለግ መሬት በሊዝ ጨረታ ማግኘት
- በቤት ልማት ለሥራ ተቋራጮችና ለአማካሪች በሚደረገው የክህሎት እና የካፒታል የመሳሪያና ማሽነሪ አቅም ማሳደጊያ ትስስር ተጠቃሚ መሆን
- ለቤት ልማት እና ትስስር ባላቸው የመንግስት ፕሮጀክቶች በሚያስፈልጉ የኢንዱስትሪ ውጤቶች የአካባቢ ግብአቶች እንዲሁም ፕሪፋብሪኬትድ ማቴሪያሎች ምርትና አቅርቦት መሳተፍ
- ለቤቶች ልማት እና ትስስር ባላቸው የመንግስት ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጉ ማሽነሪና ተሽከርካሪ አቅርቦት እንዲሆም የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት በመስጠት መሳተፍ

### ➢ በሪል እስቴት የቤት አልሚነት መሳተፍ

- በአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረት በቤቶች ልማት ፕሮግራም በአማካሪነት እና በስራ ተቋራጭነት ወይም በባለሙያነት በመቀጠር የስራ ትስስር ማግኘት

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
የዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳ/ጄኔራል
አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ
ስልክ 251115513884
ፋክስ 251115514300
ፖስታ 393
ኢሜል mfa.community@ethionet.et

በዳያስፖራ መረጃና ጥናት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ
ጥቅምት 2005 ዓ.ም.

በአገሬ ማተሚያ ቤት ታተመ